

DEREK PRINCE
MINISTRIES INTERNATIONAL

መንፈሳዊ ጽሑፍ

ኃይለኛ ጎርፍ



Word from the Word
በ ዴሪክ ፕሪንስ

ዴሪክ ፕሪንስ ነኝ፤ ከቃሉ ለእናንተ የሚሆን መልዕክት ይዤላችሁ ቀርቤአለሁ።

> አቤቱ፥ በደቡብ እንዳሉ ፈሳሾች ምርኮአችንን መልስ።
> መዝሙር 126:4

የእግዚአብሔር ሕዝብ ስለ መታደስ የጸለየት ጸሎት አለ። የኔጌቭን ምድረ በዳ የምታውቁ ከሆነ፣ እዚያ ላይ የተሳለው ምስል በጣም ግልጽ ነው። በአረብኛ “ጅረቶች” ተብሎ የተተረጎመው ቃል “ዋዲ” ይባላል። ዋዲ በዋነኝነት በመካከለኛው ምስራቅ የሚገኝ ልዩ ነገር ነው። በአመቱ አብዛኛው ጊዜ ደረቅ የሆነ የወንዝ መውረጃ ነው። ውሃ በውስጡ ይፍስ እንደነበር ማየት ይቻላል፤ ነገር ግን ለጥቂት ቀናት ዝናብ ካልዘነበ ይደርቃል፤ ቀድሞ ውሃ ፍሰት እንደነበረው የሚያሳይ ምልክት ብቻ ይቀራል።

ስለዚህ በዚያ ያለው የእግዚአብሔር ሕዝብ በዚያ ጸሎት ውስጥ ራሳቸውን በደቡብ እስራኤል በረሃ በሆኑት በኔጌቭ እንደሚገኙት ደረቅ የወንዝ መውረጃዎች አድርገው ይመለከታሉ። ነገር ግን ጸሎታቸው እግዚአብሔር በኔጌቭ እንዳሉ ፈሳሾች እንዲመልሳቸው ነው። ይህ በጣም ግልጽ የሆነ ምስል ነው፤ ምክንያቱም በኔጌቭ ዝናብ በሚዘንብባቸው በተወሰኑ ወቅቶች ዝናቡ በከፍተኛ ሁኔታ እና በብዛት ስለሚመጣ፣በጥቂት ሰዓታት ውስጥ ደረቅ የነበረው የወንዝ መውረጃ በፊቱ ያለውን ሁሉ ጠርጎ ወደሚወስድ ኃይለኛ ጎርፍ ይቀየራል፤አንዳንድ ጊዜ ድልድዮችን ጠርጎ ይወስዳል፣አልፎ ተርፎም ከባድ አደጋዎችን ያስከትላል፣መኪኖችንም ጠርጎ ይወስዳል፤ስለዚህም ከጥቂት ሰዓታት በፊት ትቢያ የለበሰ እና ድረቅ ብቻ በነበረበት ቦታ፣ አሁን የሚተምም ኃይለኛ ጎርፍ ይሆናል።

እንግዲህ በመንፈስ የሚያነሳሳ ጸሎታቸውም እግዚአብሔር ሕዝቡን በኔጌቭ ምድረ በዳ እንዳሉ ጅረቶች እንዲያድሳቸው ነው፤ምንም እንኳ የውኃ ምልክት የማይታይብን ደረቅና ትቢያ የለበስን ብንሆንም፣ እግዚአብሔር በድንገት ይጎበኘናል፤ እንቅፋቶችን ሁሉ ጠራርጎ እንደሚወስድ ኃይለኛ ጐርፍ የመንፈሱን ጉብኝት ይልካል።

© 1970 - ዴሪክ ፕሪንስ ሚኒስትሪዎች ኢትዮጵያ

መንፈሳዊ ጽሑፍ ★

ግልባጭ: WD-WFTW-113-AMH

መጨረሻ የዘመነው: 28 Oct 2026

ድህረገፅ: Derekprince.com/am/resources

